እርስዎ
የቅጥር አድልዎ ሰለባ ነዎት?

- በዘርዎ ወይም በቀለምዎ ምክንያት ከደረጃዎ ዝቅ ተደርገዋል?
- በእርግዝናዎ ምክንያት ከሥራዎ ተባርረዋል?
- ምንም እንኳን እርስዎ በጣም ብቁ እጩ ቢሆኑም ተሸከርካሪ ወንበር ስለሚጠቀሙ አንድ ኩባንያ ሊቀጥርዎ ፈቃደኛ አልሆነም?
- ዕድሜዎ 40 ወይም ከዚያ በላይ ስለሆነ ዕድገትን ተከልክለዋል?
- የመድልዎ ተግባርን በመቃወምዎ ምክንያት ከሥራዎ ተባርረዋል?

እነዚህ ወይም መሰል ሁኔታዎች እንዳጋጥምዎት የሚያምኑ ከሆነ የሥራ አድልዎ ሰለባ ሊሆኑ ይችላሉ።

እንዴት እንደምናገለግልዎት

OHREP የፌርፋክስ ካውንቲ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌን እና የፌርፋክስ ካውንቲ ፍትህ ያለበት የቤት የቤቶች ህግን የሚያስፈፅም ገለልተኛ፣ ሀቅ ፈላጊ፣ አስተዳደራዊ ድርጅት ነው። የሕግ ውክልናን አናቀርብም።

መስሪያ ቤታችን መድልዎችን በሚከተለው ሁኔታ ይዳስሳል፣

- ጉዳዮችን በመቀበል፣ በማጣራት፣ በሽምግልና፣ በምርመራ፣ በእርቅ፣ እና በአደባባይ ችሎቶች መፍታት።
- በፌርፋክስ ካውንቲ ውስጥ የመድልዎ መጠን ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ መሞከር።
- የቤቶች እና የሥራ አድልዎን ጨምሮ በሲቪል መብቶች ርዕሶች ላይ ተናጋሪዎችን እና ፕሮግራሞችን ማቅረብ።

እንዲሁም አድልዎን በተመለከተ በድረ-ገፃችን እና በጥያቄ ነፃ ህትመቶችን ማግኘት ይችላሉ።

የፌርፋክስ ካውንቲ የሰብአዊ መብቶች እና የፍትሃዊነት ፕሮግራሞች ጽ / ቤት

12000 Government Center Parkway, Suite 318
Fairfax, VA 22035-0093
ስልክ፣ 703-324-2953፣ መስማት ለተሳናቸው 711
fairfaxcounty.gov/humanrights

አንድ ፌርፋክስ ካውንቲ፣ ቪ.፣ ህትመት | ሰኔ 2018

የፌርፋክስ ካውንቲ በሁሉም የካውንቲ መርሃግብሮች፣ አገልግሎቶች እና እንቅስቃሴዎች ውስጥ የአካል ጉዳትን መሠረት ያደረገ አድልዎን ለመከላከል ቁርጠኛ ነው። በተጠየቁ ጊዜ ተመጣጣኝ የADA ማመቻቻና እና አማራጭ የመረጃ ቅርፀቶች ይቀርባሉ።

እ.ኤ.አ. መስከረም 2020 (Amharic)

የቅጥር አድልዎ

መብቶትን ይወቁ

የፌርፋክስ ካውንቲ የሰብዓዊ መብቶችና የፍትሃዊነት ፕሮግራሞች ጽሕፈት ቤት

ማንነታችን

የፌርፋክስ ካውንቲ የሰብዓዊ መብቶችና የፍትሃዊነት ፕሮግራሞች ጽሕፈት ቤት (OHREP) በሥራ ቅጥር፣ በመኖሪያ ቤት፣ በሕዝብ ማመቻቻ፣ የግል ትምህርት እና ብድር መድልዎ የሚከለክለውን የፌርፋክስ ካውንቲ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌን እና የፌርፋክስ ካውንቲ ፍትህ ያለበትን የቤቶች አሰጣጥ ህግን ያጠናክራል። OHREP በፌርፋክስ ካውንቲ ውስጥ መድልዎ እንደተፈፀመበት በሚያምን ማንኛውም ሰው የቀረቡትን አቤቱታዎች ይቀበላል፣ ይመረምራል።

ሕጉን ይወቁ

በፌርፋክስ ካውንቲ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ መሠረት፣ አራት ወይም ከዚያ በላይ ሠራተኞች ያላቸው ቀጣሪዎች፣ የሥራ ስምሪት ኤጀንሲዎች እና በፌርፋክስ ካውንቲ ውስጥ የሚሠሩ የሠራተኛ ድርጅቶች ከሚከተሉት በአንዱ የተጠበቁ ክፍሎች በአባልነታቸው መሠረት በማንኛውንም ሰው ከማድላት **የተከለከሉ ናቸው።**

- ☑ ዘር፣
- ☑ ቀለም
- ☑ ሃይማኖት
- ☑ ጾታ፣
- ☑ ወሲባዊ ዝንባሌ
- ☑ የሥርዓተ-ፆታ ማንነት
- ☑ የጋብቻ ሁኔታ
- ☑ እርግዝና
- ☑ ማጥባት ጨምሮ፣ ልጅ መውለድ ወይም ተዛማጅ የሕክምና ሁኔታዎች
- ☑ እድሜ፤
- ☑ የአካል ጉዳት
- ☑ የአርበኝነት ሁኔታ
- ☑ የመጡበት አገር

ህጉ የሚከተሉትን በተመለከተ በማንም ሰው ላይ የሥራ አድልዎ ይከለክላል፣

- ☑ ምልመላ
- ☑ ቅጥር
- ☑ እድገት
- ☑ ማሰናበት
- ☑ የሥራ ሽግግር
- ☑ የሥራ ስልጠና
- ☑ ደሞዝ
- ☑ ሌላ ማንኛውም፣ የቅጥር ደንብ፣ ሁኔታ ወይም መብት

ሰራተኞች ወሲባዊ ትንኮሳ እና የዘር ትንኮሳ ጨምሮ፣ አድልዎ እና ትንኮሳ በሌለበት አካባቢ የመሥራት መብት አላቸው። በተጨማሪም ህጉ ጥበቃ በሚደረግለት እንቅስቃሴ ውስጥ በመሳተፉ በማንኛውም ሰው ላይ የበቀል እርምጃ መውሰድን ይከለክላል፣ ይህም የመድልዎ አቤቱታ ማቅረብ እና መመስከር፣ ማገዝ ወይም በማንኛውም ምርመራ፣ ሂደት ወይም ችሎት ውስጥ መሳተፍ ያካትታል።

ቅሬታ እንዴት እንደሚቀርብ

በሕገ-ወጥ መንገድ አድልዎ ደርሶብኛል ብለው የሚያስቡ ከሆነ፣ አድልዎ ተፈጽሞብኛል ካሉበት ቀን ጀምሮ በ365 ቀናት ውስጥ ለ OHREP አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ። ቅሬታ ለማቅረብ ወይም አቤቱታ ስለማቅረብ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ፣

ይደውሉልን፣ 703-324-2953, TTY 711

የእኛን ድረ ገጽ ይጎብኙ፣
fairfaxcounty.gov/humanrights

ቢሮአችንን ይጎብኙ፣
Fairfax County Government Center
12000 Government Center Parkway, Suite 318
Fairfax, VA 22035-0093

ቅሬታ ለማስገባት ምንም ክፍያ የለም።

አድልዎ ተፈጽሞብኛል ባሉበት **በ365 ቀናት ውስጥ ቅሬታ** መቅረብ አለበት።

ቅሬታን ለማቅረብ የሚያስፈልጉ 6 ደረጃዎች

ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው በምርመራው ሂደት ውስጥ የሚከተሉትን እርምጃዎች መጠበቅ አለብዎት።

1. የመግቢያ መጠይቅ ያጠናቅቃሉ።
2. አቤቱታውን ለማዘጋጀት አንድ መርማሪ ከእርስዎ ጋር በስልክ ወይም በአካል ቀርቦ ቃለ መጠይቅ ያደርጋል።
3. የቅሬታ ቅጽ ያዘጋጃሉ እና ይፈርማሉ።*
4. መርማሪው ለምላሽ ሰጭው ያሳውቃል።
5. እውነታዎችን ለማወቅ ጥልቅ ምርመራ ይካሄዳል።
6. OHREP ማስረጃው የርስዎን ጥያቄ ይደግፍ ወይም አይደግፍ እንደሆነ ይወስናል።

* አቤቱታዎ እርስዎ እስኪፈርሙ ድረስ እንደ “ክስ” አይቆጠርም፣ እና OHREP ቅሬታውን በተመለከተበት ቀን ተቀብሎ ማህተም አድርጓል።